## ውድ የኦንላይን የቅኔ ተማሪዎቼ ለዐቢይ ጾም እንኳን አደረሳችኹ

**የዐቢይ ጾም አንደኛ ሳምንት** *ዘወረደ*

- ***ዘወረደ/ ጾመ -ሕርቃል***

*ይህ የዐቢይ ጾም የመጀመሪያ ሳምንት ዘወረደ /ጾመ ሕርቃል/ ይባላል ፡፡ ዘወረደ መሰኘቱ የዜማው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድርሰቱ ላይ ‹‹ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ›› በማለት ጌታ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን እያነሳ የሚያወድስበት ሳምንት በመሆኑ ዘወረደ ተብሏል ፡፡ ይህ ጾም ጾሙ መግቢያ የመጀመሪያ ሳምንት የምንጾመው ጾም ሲሆን ጾመ ሕርቃል የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል ፡፡ **ሕርቃል** ማን ነው? ለምንስ በስሙ ተሰየመ ?*

በ6114 ዓ.ዓ (በ614 ዓ.ም) **ኪራስ** የተባለ የፋርስ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን በመውረር ጥቃት አደረሰ ፡፡ በዚኽ ወቅት በኢየሩሳሌም ንግሥት እሌኒ በሠራችው ቤተመቅደስ ውስጥ ሲገባ ንግሥቷ በክብር አስቀምጣው የነበረው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንደ ፀሐይ ሲያበራ አገኘው ቢነካው አቃጠለው ዲያቆናቱን አሸክሞ ሌላውን ንዋየ ቅድሳት ዘርፎ 60ሺ የሚከተሉትን አቁስሎ ገድሎ 3ሺ የሚሆኑትን ማርኮ ከተማዋንም አቃጥሎ ወደ ፋርስ ባቢሎን ይመለሳል ፡፡ በዚኽ ጊዜ ከጦርነቱ ያመለጡ በየዋሻው በየጉራንጉሩ ገብተው የተሸሸጉ ተሰባስበው ከ14 ዓመት በኋላ በ628 ጩኸታቸውንና የደረሰባቸውን በደል ለክርስቲያኑ የሮም ንጉሥ **ሕርቃል** ይነግሩታል ፡፡ እርሱም ሐዋርያት ሰውን የገደለ ዕድሜያቸውን በሙሉ ይጹም ስላሉ እንዴት አደርገዋለው ለእኔ ይህ አይሆንልኝም አላቸው ፡፡ ሕዝቡም ዳዊት በመዝሙር የሰው እድሜ ቢበዛ 70/80 ነው ብሏል ፡፡ ስለዚህ እኛ የአንተን ዕድሜ ተካፍለን እንጾምልሀለን ብለው አንድ አንድ ሳምንት ደርሷቸው ጾሙን በሚገባ ጾመውታል ፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀልና የተማረኩ ክርስቲያኖች ለመመለስ ሕርቃል ጦር መዝዞ በኪራስ ላይ ተነሳበት ድል ለሕርቃል ሆነና መስቀሉ ያለበትን አጥቶ ሲቸገር መስቀሉን ሲቀብርና ዲያቆናቱን ሲያስገድል በመስኮት ሆኖ ያየቸው ከኢየሩሳሌም የተማረከች አንዲት ብላቴና አሳይታው አውጥቶ በልብሰ መንግሥቱ ጠቅልሎ ወደ ቁስጥንጥንያ ተመለሰ ፡፡ በጌታ ጾም ላይ እንዲሰየም የሆነበት ምክንያት ጾሙ የጌታ ጾም በሚጾምበት ወቅት ላይ ስለተጾመ ቤተክርስቲያን አብራ ደንግጋዋለች ፡፡ በዚህ ጊዜ ለሕርቃል ሕዝቡ ሱባኤ ይዘውለታል ፡፡ ዛሬም እኛ አምላክ ለሕርቃል የሰጠውን በጠላቶቹ ላይ ድል መንሳትን ለኛ እንዲሰጠን የምንጠይቅበት ስለሆነ የመጀመሪያውን ሳምንት በሕርቃል ተሰይሟል ፡፡

# በዐቢይ ጾም ቅኔ የሚያስነግሩ ኩነቶች

## በዚኽ ሳምንት (ዘወረደ) ቅኔ የሚያስነግሩ ኩነቶች

- ጾመ ሕርቃል
- ክርስቲያኖች ለሕርቃል መጾማቸው

## ዐቢይ ጾምን በሙሉ ከዘወረደ ጀምሮ እስከ ኆሳዕና የሚያስነግሩ ኹኔታዎች

- ከበሮና ጸናጽል ዝም ማለታቸው ፤ ከቅኔ ማኅሌት መወገዳቸው
- መቋሚያ ለአገልግሎት መዋሉ ፤ ወደላይ ወደላይ መዝለሉ
- ባሕታውያን ሱባኤ መያዛቸው እንዲኹም ቅጠል እየበሉ ፣ አሸዋ ላይ እየተኙ መጾማቸው
- ምእመናን መጾማቸው ሥጋ ፣ወተትና የወተት ተዋጽኦች አለመብላታቸው
- ከእምነቱ ውጭ ያሉ ሰዎች አለመጾማቸው

## ወርቅ የሚኾኑ ቃላት(ለሚጠሙ)

**ግእዝ** **ፍቺ**

- ጾም--------------------ጦም
- ቀኖና-------------------በቁሙ ፣ እየቀነሱ ትንሽ ትንሽ መብላት
- ትሕርምት-------------ከእኽል መከልከል
- ሱባኤ-------------------በቁሙ ፣7 ቀናት 1 ሱባኤ ፣14 ቀናት 2 ሱባኤ ፣21 ቀናት 3ሱባኤ…
- ከበሮ--------------------በቁሙ ፣በቤ/ክ ለማኅሌት አገልግሎት የሚውል
- ቀርን--------------------ከበሮ ›› ››
- ጸናጽል-----------------በቁሙ ፣በማኅሌት ከከበሮ ጋር በድምጽ ቃና 1 ኾኖ የሚያገለግል
- ምቅዋም----------------መቋሚያ ፣ሊቃውንቱ ለዝማሜ የሚጠቀሙበት በትር
- በትር--------------------በቁሙ ›› ››
- ምእመናን--------------አማኞች ፣ክርስቶስን አምነው የእርሱን አብነት የሚከተሉ
- ባሕታውያን------------ይኽን ዐለም ንቀው በገዳም የሚኖሩ መናንያን
- ባሕታውያን በጾም ወቅት የሚጠቀሙባቸው ፡-ቆጽል (ቅጠል) ፣ኆፃ (አሸዋ) ፣ገዳም (ጫካ)

**ወርቅ የሚኾኑ ቃላት (ለማይጠሙ)**

- ሞአብ ፣አማሌቅ ፣ኔባል ------የአሕዛብ አገሮች) ፣
- ተንባል---------------------------ሞስሊም
- ቅብዕ--------------ቅቤ
- ሐሊብ-------------ወተት
- ቴሮጋ--------------እርጎ
- ሥጋ---------------በቁሙ
- አንቆቅሆ----------እንቁላል

**አንጻር የሚኾኑ ቃላት**

***በጾምና ሱባኤ አንጻር የሚኾኑ***

- አዳም
- ሙሴ
- ኢያሱ
- ኤልያስ
- ወዘተ

***በዝምታ አንጻር የሚኾኑ***

- ኢሳይያስ
- ዘካርያስ
- አጋቶን
- ወዘተ የመሳሰሉት

➲ **ለጥያቄ ፡- ጳውሎስ ብርሃኔ** +251915642585